# በአለምአቀፍ ቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን የተዘጋጀ የቤተመጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች የስነ-ምግባር ደንብ

***ማውጫ***

***መግቢያ***


1. *መረጃዎችን በቀላሉ ስለማግኘት*
2. *ባለሙያዎች ለግለሰብና ለማህበረሰብ ስላለባቸው አላፊነት*
3. *ስለግል ህይወት መከበርና መጠበቅ፣ ስለግል ምስጢርና ግልጽነት*
4. *ያለምንም ክልከላ መረጃን ስለማግኘትና ምሁራዊ ባለመብትነት*
5. *ከአድልዎ ነጻ ስለመሆን፣ግላዊ ታማኝነት እና ከፍ ያለ ሙያዊ ብቃት*
6. *በአሠሪና ሠራተኛ መካከል እና በሠራተኞች መካከል ስላለ ግንኙነት*

***ተጨማሪ ጥናቶች***


***መግቢያ***

*ይህ የሥነ-ምግባር ደንብ ለቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (information) ሠራተኞች ሥነ-ምግባራዊ ማስገንዘቢያ እንዲሆናቸው የተዘጋጀ መምሪያ ሆኖ በተጨማሪም የቤተ-መጻህፍትና የመረጃ ማህበራት የአሰራር ደንቦቻቸውን በሚያዘጋጁበት ወይም የተዘጋጁ ካሏቸው እንደገና ከልሰው በሚያዩበት ወቅት ይህን የሥነ-ምግባር ደንብ ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡት ታስቦ የተዘጋጀ ነው።*

*የሥነ-ምግባር ደንቡን ግብ እንደሚከተለው ለመግለጽ ይቻላል፡-*

- *የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (information) ሠራተኞች የአሰራር ፖሊሲዎቻቸውን በሚቀርጹበትና አሻሚ ሃሳቦች በሚያጋጥሟቸው ወቅት በሙያው መርሆዎች ላይ መላልሰው እንዲያስቡባቸው ለማበረታታት፤*
- *ሙያዊ ግለ-ግንዛቤን ለማሻሻል፤እና*
- *ለተጠቃሚዎችና ለህብረተሰቡም በአጠቃላይ ግልጽ አሰራርን ለማስተዋወቅ።*

*ይህ ደንብ በስራ ላይ ያሉ ደንቦችን እንዲተካ ወይም የሙያ ማህበራት በምርምር፣ በምክክር እና ትብብር ላይ ተመስርተው የራሳቸውን ደንብ ለማርቀቅ ያላቸውን ሙያዊ ግዴታ ለማስቀረት ታስቦ የተዘጋጀ አይደለም። ሁሉም ሙሉ በሙሉ በእነዚህ ደንቦች እንዲገዙም አይጠበቅም።*

*ይህ ደንብ የቤተ-መጻህፍት ባለሙያነት ከመሰረቱ መረጃን ለተመረኮዘ ሙያዊ ስራ በዕሴት የበለጸገ አቀራረብ ያለው ስነ-ምግባራዊ ሙያ ነው በሚል እምነት የተዘጋጀ ነው።*

*ይህ ደንብ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከማህበረሰቦች ዕድገት እየተወሳሰበ መምጣት ጋር በሰው ልጆች በኩል እሳቤዎችንና መረጃዎችን ለመለዋወጥ ያለው ፍላጎት በዚያው መጠን የበለጠ ከፍ እያለ መምጣቱንና ይህ ደግሞ የቤተ-መጻህፍቶችንና የቤተ-መጻህፍትን ሙያ አስፈላጊነት ከመቼውም ጊዜ በላይ ጨምሮታል በሚል እምነት የተዘጋጀ ነው።*

*ይህ ደንብ በዚህ በሰለጠነ ዘመን ውስጥ ቤተ-መጻህፍትንና የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችን ጨምሮ የመረጃ ተቋማትና ባለሙያዎች ሚና መረጃዎች በተገቢው እንዲመዘገቡና እና ሁሉንም በሚወክል ደረጃ እንዲገኙ ለማስቻል የሚደረገውን ጥረት ከፍ በማድረግ ረገድ መተባበርና እነዚህንም መረጃዎች ህብረተሰቡ በቀላሉ እንዲያገኛቸው ማስቻል ነው በሚል እምነት የተዘጋጀ ነው።*

ይህ ደንብ የመረጃ አገልግሎትን ለማህበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ማዋል የቤተ-መጻህፍት ሙያ መሰረታዊ መርህ መሆኑንና ይህንንም ተከትሎ የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎች ማህበራዊ አላፊነት አለባቸው በሚል እምነት የተዘጋጀ ነው።

ይህ በሰው ልጆች መረጃዎችንና ሃሳቦችን ለመካፈል ባላቸው ጽኑ ፍላጎት ላይ ያለው እምነት መረጃን የማግኘት መብትን እንደመብት መቀበልን ያስከትላል። የሰብአዊ መብቶች ጽንሰ-ሃሳቦች በተለይም በተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች (1948) ላይ እንደተመለከቱት ሁላችንም የሌሎችንም ሰብአዊነት እንድንቀበልና መብቶቻቸውንም እንድናከብር ግዴታ ይጥሉብናል። በተለይም የድንጋጌው አንቀጽ 19 የራስን ሃሳብ በነጻነት የመያዝና ሃሳብን የመግለጽ እንዲሁም መረጃን የማግኘት መብትን ለሁሉም የሰው ልጆች ስለማጎናጸፍ ይደነግጋል።

ይኸው አንቀጽ 19 “በማናቸውም ዓይነት የሚዲያ ዘዴ እና በድንበር ሳይወሰን ሁሉም ሰው መረጃዎችንና ሃሳቦችን የመፈለግ፣ የመቀበልና የማግኘት” መብት ያለው ስለመሆኑ በማያሻማ ሁኔታ ያስቀመጠ ሲሆን ይህ ደግሞ ለቤተ-መጻህፍትና ለዘመናዊውና በፍጥነት እያደገ ለመጣው የቤተ-መጻህፍት ሙያ መሪ ሃሳብ ነው። አለም-አቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን በመግለጫዎቹ፣ በማኒፌስቶዎቹና እንዲሁም በፖሊሲና ቴክኒካል ዶኩሜንቶቹ በመረጃ (information) ሥራዎች ላይ ያለውን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ጥረት አድርጓል። በዚህም ሥራ አማካይነት ስለመረጃ መብት ጉዳይና ይህም በሙያውና በአጠቃላይም በህብረተሰቡ በኩል ስላለው አስፈላጊነት አመልክቷል። በመረጃ መብት ላይ እየተደረገ ያለው አትኩሮት በአንጻሩ ደግሞ የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (information) ሠራተኞች አግባብነት ያላቸውን ህጎች በመርህ ላይ ተመስርተው ሂስ እንዲያቀርቡባቸውና በተጨማሪም በመሰረታዊ ህጎችና እንዲሁም በአፈጻጸማቸው ላይ ተገቢውን ምክር እንዲሰጡና እንደአግባብነቱም እነዚሁ እንዲሻሻሉ በቀዳሚነት ለመቆም እንዲዘጋጁ ሃላፊነት ይጥልባቸዋል።

በዚህ የሥነ-ምግባር ደንብ ላይ የተመለከቱት መሰረተ ሃሳቦች በባለሙያዎች ምግባር ላይ አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮችን ስለመስጠት በመግቢያው ላይ በተመለከቱት መሰረታዊ መርሆዎች ላይ የሚመረኮዙ ናቸው። አለም-አቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን እነዚህ መሰረታዊ መርሆዎች በተመሳሳይ በሚዘጋጁ ሌሎች የሥነ-ምግባር ደንቦች ውስጥ እንደቁልፍ መርሆዎች ሊያገለግሉ ይችላሉ ብሎ የሚያምን ቢሆንም ዝርዝር የደንቦቹ ሃሳቦች እንደየህብረተሰቡ እና ደንቦቹ በተግባር ላይ እንደሚውሉባቸው ማህበረሰቦች ሊለያዩ እንደሚችሉ ያምናል። የሥነ-ምግባር ደንቦችን ማዘጋጀት የአንድ የሙያ ማህበር ወሳኝ ተግባር እንደሆነው ሁሉ በሥነ-ምግባር ጉዳዮች ላይ አጥብቆ ማሰላሰል ለባለሙያዎች እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። አለም-አቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን አባል ማህበራትና ተቋማት እንዲሁም ሁሉም የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎች ይህን የፌዴሬሽኑን የሥነ-ምግባር ደንብ ከጥቅም ላይ እንዲያውሉት ይጋብዛል።

የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን ይህን የሥነ-ምግባር ደንብ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ እንደገና ያሻሽለዋል።

1. ***<u>መረጃዎችን በቀላሉ ስለማግኘት</u>***

ለግላዊ መሻሻል፣ ለትምህርት፣ ለባህላዊ ዕድገት፣ ለመዝናኛ፣ ለኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እና በበቂ መረጃ ላይ ለተመሰረተ ተሳትፎና ለዲሞክራሲ ማበብ መረጃዎች ለሁሉም በቀላሉ እንዲገኙ ማድረግ የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች ቁልፍ ሚና ነው።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች ማናቸውንም መረጃዎችና ሃሳቦች በቀላሉ እንዳይገኙ የሚደረግን ክልከላ ወይም ገደብ በተለይም በመንግስታት፣ በሃይማኖት ድርጅቶችና በሌሎች የብዙሃን ማህበራት የሚደረግን ቀዳሚ-ምርመራ (ሳንሱር) አጥብቀው ይቃወማሉ።

አገልግሎቶቻቸውን ለብዙሃኑ ማህበረሰብ የሚያቀርቡ የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች ስብስቦቻቸውንና አገልግሎቶቻቸውን ለተጠቃሚዎች ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ በሆነ መንገድ ለማቅረብ ተገቢውን ጥረት ሁሉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የአባልነት ወይም የአስተዳደር ወጪ ክፍያዎችን ማስከፈል ግድ በሚሆን ጊዜ በተቻለ መጠን ክፍያዎቹ አነስተኛ እንዲሆኑና በተለያየ ምክንያት የማህበራዊ ተሳትፎ አቅማቸው ውስን የሆኑ የህብረተሰቡ ክፍሎች አገልግሎቱን ከማግኘት እንዳይገለሉ ተጨባጭ መፍትሄዎችን መሻት ያስፈልጋል።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች የአገልግሎቶቻቸው ተጠቃሚዎች ወይም ወደፊት ሊጠቀሙ የሚችሉ ሰዎች ይህ አገልግሎት ስለመኖሩ እንዲያውቁ ወይም ስለአገልግሎቱ ሁኔታ ለማወቅ እንዲችሉ ስለ ስብስቦቻቸውና አገልግሎታቸው ተገቢውን የማስተዋወቅ ሥራ መስራት ይኖርባቸዋል። የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች ስብስቦቻቸውንና አገልግሎቶቻቸውን ለሁሉም በቀላሉ ለማድረስ እጅግ ውጤታማ የሆኑ መንገዶችን መጠቀም ይችላሉ። ይህንን ለማድረግ የቤተ-መጻህፍትና የሌሎች የመረጃ (Information) ተቋማት ድረ-ገጾች (websites) ዓለም-አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ መረጃዎች በቀላሉ የሚገኙባቸው ሆነው መደራጀታቸውንና መረጃዎቹንም ለማግኘት ምንም ዓይነት ዕቀባ አለመኖሩን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

## 2. ባለሙያዎች ለግለሰብና ለማህበረሰብ ስላለባቸው አላፊነት

አሳታፊነትን ለማበረታታትና መድልዎን ለማጥፋት የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች መረጃን በቀላሉ የማግኘት መብት ያልተገደበ  መሆኑንና አገልግሎቱ የእድሜ፣ የዜግነት፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ የአካል ወይም የአዕምሮ ችሎታ ደረጃ፣ የጾታ፣ የትምህርት፣ የገቢ መጠን፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የዘር፣ ወይም የሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግበት ለሁሉም እንዲደርስ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች የቋንቋው ተናጋሪዎች ቁጥር አነስተኛ የሆኑባቸውን ማህበረሰቦች ማክበር የሚገባቸው ሲሆን በራሳቸው ቋንቋ መረጃዎችን እንዲያገኙ መስራት ይኖርባቸዋል።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች ተጠቃሚዎቻቸው ማንነታቸውን ሳይገልጹ መረጃዎችን ማግኘት እንዲችሉ አድርገው አገልግሎቶቻቸውን ማደራጀትና ተጠቃሚዎች በሚያደርጉት የመረጃ ፍለጋም በአግባቡ ሊረዷቸው ይገባል።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች የተጠቃሚዎች የማንበብ ችሎታ እንዲያድግ መጣር ይገባቸዋል። በህብረተሰቡ ውስጥ የመረጃ (Information) እውቀት እንዲዳብር በተለይም መረጃን ለይቶ የማግኘት፣ የመመዘን፣ የማደራጀትና የመፍጠር፣ የመጠቀምና ለሌሎች የማስተላለፍ ችሎታ እንዲያድግ በተቻላቸው ሁሉ መስራት ይጠበቅባቸዋል። እንዲሁም ስነ-ምግባራዊ የመረጃ አጠቃቀምን በማበረታታት የሌሎችን የስራ ውጤቶችን እንዳለ ገልብጦ የራስ ስራ ማስመሰልንና ሌሎች መሰል መረጃዎችን ካላግባብ የመጠቀም አዝማሚያዎችን ለማስወገድ የሚደረገውን ጥረት ማገዝ ይጠበቅባቸዋል።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች የአዋቂዎችን መረጃ የማግኘት መብት በማይጎዳ መልኩ ለአቅመ-አዳም ወይም ለአቅመ-ሄዋን ያልደረሱ ህጻናትን መብት ጥበቃ ማክበር ይኖርባቸዋል።

## 3. ስለግል ህይወት መከበርና መጠበቅ፣ ስለግል ምስጢርና ግልጽነት

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች የተጠቃሚዎችን የግል ህይወት ማክበርና መጠበቅ እንዲሁም በግለሰቦችና በተቋማት መካከል የሚደረግን የመረጃ ቅብብሎሽ ነጻነትና ምስጢራዊነት ማክበር ይገባቸዋል።

በቤተ-መጻህፍትና በተጠቃሚዎች መካከል ያለው ግንኙነት የተጠቃሚዎችን ምስጢራዊነት በማክበር ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች የተጠቃሚዎች መረጃዎች ከታቀደው የመረጃ ቅብብሎሽ ሰንሰለት ውጪ ባልታቀደ ሁኔታ ለሌሎች እንዳይደርሱ አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች የመንግሥታት፣ የአስተዳደሮችና የንግድ ክፍሎች አሰራሮች ከህዝብ ዕይታ ያልተደበቁ እና ግልጽ አሰራር የሰፈነባቸው እንዲሆኑ የሚደረጉ ጥረቶችን መደገፍና በጥረቱ ውስጥም መሳተፍ ይገባቸዋል። ያልተገቡ አሰራሮች፣ የሙስና ተግባራት እና ወንጀሎች መጋለጣቸው ህብረተሰቡን የሚጠቅም ተግባር ስለሆነ ይህንንም መደገፍ ይገባቸዋል።

4. <u>ያለምንም ክልከላ መረጃን በቀላሉ ስለማግኘትና ስለምሁራዊ ሃብት ባለቤትነት</u>

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች ግብ የቤተ-መጻህፍት ተጠቃሚዎች በማናቸውም ዓይነት የመገናኛ ዘዴም ይሁን ቅርጽ በተቻለ መጠን ያለምንም ክልከላ መረጃዎችን በቀላሉ እንዲያገኙ ማስቻል ነው። ይህም መረጃዎች በቀላሉ እንዲገኙ ለማስቻል የሚደረጉ ተነሳሽነቶችን በመርህ ደረጃ መደገፍን ያካትታል።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች ሚዛናዊ፣ ፈጣን፣ ውድ ያልሆነ፣ እና ውጤታማ የመረጃ አቅርቦት ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ማስቻል ዓላማቸው ነው።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች የቅጂ መብቶች (copy rights) ጥበቃ ለቤተ-መጻህፍት አገልግሎት ሲባል በልዩ ሁኔታ እንዲታይ መታገል ሙያዊ ሃላፊነታቸው ነው።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች የፀሃፊዎች፣ የአታሚዎች እና የቅጂ መብቶች ጥበቃ ያላቸው የፈጠራ ሰዎች አጋሮች ናቸው። የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና የመረጃ (Information) ሠራተኞች የፀሃፊዎችንና የሌሎች የፈጠራ ሰዎችን የምሁራዊ ሃብት ባለቤትነት መብቶችን የሚገነዘቡ ከመሆኑም በላይ እነዚህ መብቶቻቸው እንዲከበሩላቸው ተገቢውን ጥረት ሁሉ ያደርጋሉ።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች በተጠቃሚዎች ወገን ሆነው ተጠቃሚዎች የምሁራዊ ሃብት ውጤቶችን በቀላሉ ማግኘት የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት የሚኖርባቸው ሲሆን በምሁራዊ መብት ጥበቃ ህጎች አስተዳደር አማካይነት የምሁራዊ ሃብት ውጤቶችን በቀላሉ በማግኘት ላይ አላስፈላጊ ገደብ ወይም ክልከላ እንዳይኖርና የምሁራዊ ባለቤትነት ፈቃዶች ቤተ-መጻህፍት በህግ ያገኙትን የመጠቀም መብት የማይጻረሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች መንግሥታት በምሁራዊ ሃብት ባለቤቶችና እነርሱኑ በሚያገለግሉ እንደቤተ-መጻህፍት ባሉ ተቋማት መካከል ያለውን ፍላጎት በሚዛናዊነት ሊያገለግል የሚችል የምሁራዊ መብት ጥበቃ ሥርዓት እንዲያወጡ ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች የቅጂ መብቶች ጥበቃ የክልከላ ድንጋጌዎች ውሱን እንዲሆኑና በማህበረሰቡ እጅ የገባ መረጃ በህብረተሰቡ እጅ እንዲቆይና ነጻ እንዲሆን መታገል ይገባቸዋል።

5. <u>ከአድልዎ ነጻ ስለመሆን፣ግላዊ ታማኝነት እና ከፍ ያለ ሙያዊ ብቃት</u>

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች በሚይዟቸው ስብስቦች፣ አገልግሎታቸው ለሁሉም ክፍት በሚሆኑበት ሁኔታ እና እንዲሁም በአገልግሎታቸው ገለልተኛና ከወገናዊነት የጸዳ አቋም መያዝ ይገባቸዋል። ገለልተኛነት ሚዛናዊ የሆነ ስብስብ ለመያዝና አድልዎ የሌለበትና መረጃን ለሁሉም በእኩልነት በቀላሉ እንዲገኝ የሚያስችል ሁኔታ ለማመቻቸት ይረዳል።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች በስብስቦቻቸው መረጣ፣ አደረጃጀት፣ ጠብቆ ማቆየት፣ አቅርቦት እና መረጃዎችን የሚያስተላልፉበትን ሁኔታ አስመልክቶ ፖሊሲዎቻቸውን በግልጽ ማመልከትና በህትመት መልክ ለህብረተሰቡ ማቅረብ ይገባቸዋል።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች በግላዊ እምነታቸውና በሙያዊ ሃላፊነታቸው መካከል ያለውን ልዩነት በአጽንዖት መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ገለልተኝነታቸውን ወደጎን በማድረግ የግል ፍላጎታቸውንና የግል እምነታቸውን አያራምዱም።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች ለሌሎች ተጠቃሚዎች ያላቸውን ገለልተኝነት እስካልተጻረረ ድረስ በሚሰሩበት ሥፍራ ሃሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ መብት አላቸው።

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች የቤተ-መጻህፍት ሙያን በቀጥታ ሊጎዱ በሚችሉ በቤተ-መጻህፍት አቅርቦቶች ግዥዎች፣ በቤተ-መጻህፍት የሥራ ቦታዎች ምደባና ሹመት እና በቤተ-መጻህፍት ውሎችና ፋይናንስ አስተዳደር ላይ የሚፈጸሙ ሙስናዎችን በጽኑ መዋጋት ይኖርባቸዋል::

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን ጠብቆ በማቆየትና በየጊዜው በማዳበር በሙያቸው ላይ የላቀ ብቃት ይዘው ለመዝለቅ መጣር ይጠበቅባቸዋል:: በተጨማሪም በሙያቸው ከፍተኛ ደረጃ ያለውን የአገልግሎት ጥራት ደረጃ ለማስመዝገብ ማለምና በዚህም የሙያውን በጎ ገጽታ ከፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል::

## 6. በአሠሪና ሠራተኛ መካከል እና በሠራተኞች መካከል ስላለ ግንኙነት

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች ከሙያ ባልደረቦቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት በሚዛናዊነትና በመከባበር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ ይገባቸዋል::

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች በማናቸውም ዓይነት የሥራ ቅጥር ወቅት ዕድሜን፣ የፖለቲካ አመለካከትን፣ የአካል ወይም የአዕምሮ ብቃትን፣ ጾታን፣ የጋብቻ ሁኔታን፣ የዘር፣ ወይም የሃይማኖት ሁኔታን የተመረኮዘ ማግለልን ይቃወማሉ::

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች በተመሳሳይ የሥራ መደብ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወንዶችና ሴቶች እኩል ክፍያና ጥቅማ ጥቅም እንዲያገኙ ሳያሰልሱ ያሳስባሉ::

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች ያላቸውን ሙያዊ ልምድ ለሥራ ባልደረቦቻቸው ያካፍላሉ፤ ወደሙያው አዲስ የሚመጡ ባለሙያዎችንም ወደሙያው ማህበረሰብ ሳይቸገሩ እንዲቀላቀሉና ክህሎታቸውን ማሳደግ እንዲችሉ ይደግፋሉ:: በሙያ ማህበራቸው ውስጥ በንቃት መሳተፍና እንዲሁም በሙያ ጉዳዮች ላይ ምርምር ማድረግና ስራዎቻቸውንም ለህትመት ማብቃት ይጠበቅባቸዋል፡፡

የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ (Information) ሠራተኞች ክብራቸውንና መልካም ስማቸውን የሚገነቡት በሙያዊ ብቃታቸውና በሥነ-ምግባራቸው ብቻ ነው፡፡ ያልተገባ መንገድ ተጠቅመው ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር ፉክክር ውስጥ አይገቡም፡፡

## ተጨማሪ ጥናቶች


- The Ethics of Librarianship. An International Survey. Ed. By Robert W. Vaagan with an introduction by Alex Byrne. München: Saur 2002 VI, 344 p.
- Gebolys, Zdzislaw, Jacek Tomaszczyk: Library Codes of Ethics Worldwide. Anthology. Berlin: Simon 2012. 267 p.
- Professional Codes of Ethics for Librarians. IFLA-Committee on Freedom of Access to Information and Free Expression (FAIFE). Link (19.03.2012)
- Sturges, Paul: Doing the Right Thing. Professional ethics for information workers in Britain. In: New Library World. 104, 2003, n. 1186, p. 94-102. Link (19.03.2012).
-


ይህ ጽሁፍ በሎይዳ ጋርሲያ-ፌቦ፣ አን ሁስታድ፣ኸርማን ሮሽ፣ፖል ስታርጅስ፣ አሜሊ ቫሎቶን ተዘጋጅቶ በአለም-አቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን ከፍተኛ አመራር ቦርድ እ.ኤ.አ. በኦገስት 2012 የጸደቀ ነው፡፡